**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የቤተሰብ ፍርድ ቤት**
**የቤት ውስጥ ዝምድናዎች (Domestic Relations) ቅርንጫፍ**

**Complaint for Annulment**

______________________________
ስምዎን ጎላ አድርገው ይጻፉ

______________________________
የጎዳና አድራሻ

______________________________
ከተማ፣ ስቴት እና ዚፕ ኮድ

☐ ተተኪ አድራሻ፤ ንዝነዛ ወይም ጉዳት ፈርተው፣ የሌላን ሰው አድራሻ ጽፈው ከሆነ በሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።

ከሳሽ፣

v.

______________________________
የባለቤትዎን ስም ጎላ አድርገው ይጻፉ

______________________________
የጎዳና አድራሻ

______________________________
ከተማ፣ ስቴት እና ዚፕ ኮድ

ተከሳሽ

_____DRB ________

ተዛማጅ ጉዳዮች፤

______________________________

______________________________

**ጋብቻን ለማፍረስ የቀረበ ክስ**
**የሕጻን ድጋፍን አስመልክቶ እርምጃ** ☐ አዎ ☐ አይ

እኔ፣ ____________________________፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ከሳሽ ስሆን፣ የሚከተለውን እያልኩኝ ነው
ስምዎን ጎላ አድርገው ይጻፉ

**1. ይህ ፍርድ ቤት ጋብቻዬን ለማፍረስና በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን አለው፣ ምክንያቱም፤** [በሚመለከትዎ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ እኔ በአሁኑ ወቅት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪ ነኝ።

☐ እኔና ባለቤቴ የተጋባነው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ነበር።

2. **እኔና ባለቤቴ የተጋባነው፤** [በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ በጋብቻ ስነስርዓት በ _______________ ፣ በ _____________________ ውስጥ ነበር።
ቀን ከተማና ስቴት

☐ በባህላዊ ህግ በ _____________ ላይ ወይም አካባቢ፣ በ ________________ ውስጥ ነበር
ቀን ከተማና ስቴት

3. **ጋብቻዬ መፍረስ ያለበት ምክንያት፤** [በሚመለከቱዎ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ባለቤቴን ባገባሁበት ወቅት ላይ፣ አንዳችን ከሌላ ሰው ጋራ ተጋብተን ነበር።

☐ ባለቤቴን ባገባሁበት ወቅት፣ አንዳችን ቀውሰን ነበር፣ እና ስለ ቀውስነቱ ካወቅኩኝ በኋላ፣ ሁለታችን እንደ ባልና ሚስት አንድ ላይ በፍላጎታችን መኖሩን አልቀጠልንም።

☐ እኔ ባለቤቴን ያገባሁት ባለቤቴ በሃይል አስገድዶ/ዳኝ ወይም አታሎ/ላኝ ነው።

☐ ባለቤቴን ባገባሁበት ወቅት፣ ዕድሜዬ ከ 16 ዓመት በታችና፣ እኔ 16 ዓመት ከሞላሁኝ በኋላ፣ ሁለታችን እንደ ባልና ሚስት አንድ ላይ በፍላጎታችን መኖሩን አልቀጠልንም።

4. **የጋብቻ ስሜን አስመልክቶ የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [አንድ ይምረጡ]

☐ ባለቤቴን ካገባሁኝ በኋላ ስሜን አልቀየርኩኝም።

☐ ባለቤቴን ካገባሁኝ በኋላ ስሜን ቀይሪያለሁኝ። ወደ የድሮ ስሜ ልመለስ አልፈልግም።

☐ ባለቤቴን ካገባሁኝ በኋላ ስሜን ቀይሬ ነበር እና ስወለድ ወደ ተሰጠኝ ስም ወይም ከማግባቴ በፊት ተጠቅሜበት ወደ ነበረ ሕጋዊ ስም መመለስ እፈልጋለሁኝ። ይህንን ጥያቄ ያቀረብኩበት ምንም ዓይነት ሕገወጥ ወይም የማጭበርበሪያ ምክንያት የለኝም። የምመለስበት የቀድሞ ስሜ የሚከተለው ነው፤

______________________________________________________________
ፍርድ ቤቱ ሊመልስልዎ የሚፈልጉትን ስም ጎላ አድርገው ይጻፉ

## በትዳር ወቅት የተካበተ ንብረት እና ዕዳ

5. **በትዳሪው ወቅት ያካበትኩትን ንብረት አስመልክቶ የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ እኔና ባለቤቴ በትዳሩ ወቅት የተካበተ ንብረት የለንም።

☐ እኔና ባለቤቴ በትዳሩ ወቅት የተካበተ ንብረት ሊኖረን ይችል ይሆናል፣ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ እንዲያከፋፍለን ወይም እንዲያድለን እየጠየኩኝ አይደለሁም።

☐ እኔና ባለቤቴ በትዳር ወቅት የተካበተውን ንብረት  አስመልክቶ በጽሑፍ የተዘጋጀ ውል አለን፣ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በትዳሩ ወቅት የተካበተ ያሆነ ንብረት እንዲያከፋፍለን ወይም እንዲያድለን እየጠየኩኝ አይደለሁም።

☐ እኔና ባለቤቴ ፍርድ ቤቱ እንዲያከፋፍለን ወይም እንዲያድለን የምጠይቀው፣ በትዳር ወቅት የተካበተ ንብረት አለን። በመሆኑም በተያያዥ ሰነድ A ላይ የተጠየቀን መስፈርት የሚያሟላ ተጨማሪ መረጃ ሞልቼ አንድ ላይ አያይዤው፣ በክሴ ጋራ አብሬ አንድ ላይ አስገብቼዋለሁኝ።

☐ እኔና ባለቤቴ በትዳር ወቅት የተካበተ ንብረት ይኑረን አይኑረን እርግጠኛ አይደለሁም።

6. **በትዳሬ ወቅት ስለተካበተ ዕዳ የሚከትለውን እላለሁኝ፤** [አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ባለቤቴ እና እኔ በትዳሩ ወቅት የተካበተ ዕዳ የለንም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ በትዳሩ ወቅት የተካበተ እዳ ሊኖረን ይችል ይሆናል፣ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ተጠያቂ ማን እንደሆነ እንዲወስን እየጠየኩኝ አይደለሁም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ በትዳር ወቅት የተካበተውን ዕዳ  አስመልክቶ በጽሑፍ የተዘጋጀ ውል አለን፣ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተጠያቂ ማን እንደሆነ እንዲወስን እየጠየኩኝ አይደለሁም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ፍርድ ቤቱ፣ ተጠያቂ ማን እንደሆነ እንዲወስን የምጠይቀው፣ በትዳር ወቅት የተካበተ ዕዳ አለን። በመሆኑም በተያያዥ ሰነድ A ላይ የተጠየቀን መስፈርት የሚያሟላ ተጨማሪ መረጃ ሞልቼ አንድ ላይ አያይዤው፣ በክሴ ጋራ አብሬ አንድ ላይ አስገብቼዋለሁኝ።

☐ ባለቤቴና እኔ በትዳር ወቅት የተካበተ ዕዳ ይኑረን አይኑረን እርግጠኛ አይደለሁም።

## አበል (Alimony)

7. **ፍርድ ቤቱ ጋብቻዬን እንዳፈርስ ላቀረብኩት ጥይቄ ፈቃዱን እስከሚሰጠኝ ድረስ፣ ከባለቤቴ በግዚያዊነት ደረጃ እንዳገኘው ስለምፈልግ የገንዘብ እርዳታ የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ጊዝያዊ የገንዘብ እርዳታ ያስፈልገኛል፣ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ይህንን እንዲፈቅድልኝ የተለየ ማመልከቻ ("ግዚያዊ አበል መጠየቂያ ማመልከቻ") አስገባለሁኝ።

☐ በአሁኑ ወቅት ግዚያዊ የገንዘብ እርዳታ አያስፈልገኝም።

8. **ስለ አበል የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ አበል ከባለቤቴ እፈልጋለሁኝ፣ ባለቤቴ አበል ለኔ የመክፈል አቅም አለው/አላት።

☐ ባለቤቴ አበል እንዲከፍለኝ አልፈልግም።

## ጥበቃ (Custody)

9. **ከ 18 ዓመት በታች ስላለ(ሉ) ልጃችን(ጆቻችን) የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) የሉንም።

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) አሉን፣ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በአሁኑ ወቅት ጥበቃ ለማን እንደሚሰጥ እንዲወስንልን አልፈልግም።

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) አሉን፣ ቢሆንም የልጆቹን ጥበቃ አስመልክቶ በጽሑፍ የተዘጋጀ ውል ስላለን፣ ፍርድ ቤቱ በአሁኑ ወቅት ጥበቃ ለማን እንደሚሰጥ እንዲወስንልን አልፈልግም።

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) አሉን፣ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ጥበቃ ለማን እንደሚሰጥ እንዲወስንልን እፈልጋለሁኝ። በተያያዥ ሰነድ B ላይ የተጠየቀን መስፈርት የሚያሟላ ተጨማሪ መረጃ ሞልቼ አንድ ላይ አያይዤው፣ በክሴ ጋራ አብሬ አንድ ላይ አስገብቼዋለሁኝ።

## የልጅ ቀለብ/ድጋፍ

**10. ባለቤቴ እድሜያቸው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በታች ወይም ለአቅመ አዳም የደረሱ ስንኩላን ልጃችን(ጆቻን) ድጋፍ የሚሆን ገንዘብ የመክፈል ሕጋዊ ሓላፊነት አለበት(አለባት)**

**11. የልጅ ቀለብ/ድጋፍ ጥያቄዬን አስመልክቶ የሚከተለውን እላለሁኝ፤** [በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) የሉንም ወይም በአንድ ላይ የነበሩን ልጆች ከ 21 ዓመት በላይ ናቸው እንዲሁም ለአቅመ አዳም የደረሱ ስንኩላን ልጆች አይደሉም።

☐ ባለቤቴና እኔ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ በአንድ ላይ የወለድናቸው ልጆች (ተወልደው ወይም በጉዲፈቻ በኩል) አሉን፣ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በአሁኑ ወቅት የልጅ ቀለብ/ድጋፍ እርዳታ እንዲወስንልን አልፈልግም።

☐ ባለቤቴና እኔ ስለ ልጅ ድጋፍ/ቀለብ ስምምነት ላይ ደርሰናል። ይህ ስምምነት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የልጅ ድጋፍ መመሪያን የተከተለ ሲሆን፣ እንዲሁም/ወይም አግባብነትን የጠበቀና ፍትሓዊ ነው።

☐ ፍርድ ቤቱ የልጅ ድጋፍ/ቀለብ እንዲወስንልን እፈልጋለሁኝ። *እናም* በተያያዥ ሰነድ C ላይ የተጠየቀን መስፈርት የሚያሟላ ተጨማሪ መረጃ ሞልቼ አንድ ላይ አያይዤው፣ በክሴ ጋራ አብሬ አንድ ላይ አስገብቼዋለሁኝ።

## ተያያዥ ሰነዶች

**12. የሚከተለው(ሉት)ን ተያያዥ ሰነድ(ዶች) አብሬ ጨምሪያለሁኝ፤** [በሚመለከቱዎ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ምንም የተያያዙ ሰነዶ የሉም
☐ ተያያዥ ሰነድ A (በትዳር ወቅት የተካበተ ንብረት፣ ዕዳ ወይም አበል)
☐ ተያያዥ ሰነድ B (የልጅ ጥበቃ)
☐ ተያያዥ ሰነድ C (የልጅ ድጋፍ/ቀለብ)

## እፎይታን (Relief) መጠየቅ

**እኔ፣ ፍርድ ቤቱን የሚከተሉትን በክብር እጠይቃለሁኝ፤** [በሚለከቱዎ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ እንዲፈርስ ላቀረብኩት ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ይሰጠኝ።

☐ በትዳሩ ወቅት የተካበተ ንብረትንና/ወይም በትዳሩ ወቅት የተካበቱ ዕዳዎችን ተገቢነት፣ ፍትሓዊነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲያካፍለን።

☐ አበልን ፍትሓዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲወስን።

☐ ጥበቃን የልጁ(ጆቹ)ን ጥቅም በበለጠ ለማስጠበቅ በሚቻልበት መንገድ እንዲወስን።

☐ ማመልከቻዬን ካስገባሁኝ በኋላ በ 45 ቀኖች ውስጥ ጥያቄዬን በችሎት ፊት ማቅረብና ለሌላኛው ወላጅ፣ የችሎቱን ቀንና ሰዓት ያለው የችሎትና የእንዲገኙ ትእዛዝ (Notice of Hearing and Order Directing Appearance)(“NOHODA”) የማስታወቅያ ማውጣት።

☐ የልጅ ቀለብ/ድጋፍ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የልጅ ቀለብ/ድጋፍ መመሪያዎች (Child Support Guideline of the District of Columbia) እና የሚከተሉትን ጨምሮ፣ በሌሎች የሚመለከታቸው ሕጎች መሰረት መወሰን፤ [በሚለከቱዎ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ]

- ☐ ወቅታዊ የልጅ ቀለብ/ድጋፍ (ከዛሬ ጀምሮ ያለውንና ለወደፊት የሚቀጥለውን ድጋፍ)
- ☐ ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ የልጅ ቀለብ/ድጋፍ (ከዚህ ቀን በፊት ለነበረ ግዜ ድጋፍ)
- ☐ የህክምና ድጋፍ

☐ በጽሑፍ የተዘጋጀ ውል እንዳለን ይታወቅልኝ። ፍርድ ቤቱ እንደሚከተለው እንዲያደርግ እጠይቃለሁኝ፤ [በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

- ☐ እንደ የትእዛዙ ክፍል፣ እኛ የነበረን የጽሑፍ ውል *አብሮ ይግባ*።
- ☐ እንደ የትእዛዙ ክፍል፣ እኛ የነበረን የጽሑፍ ውል *አብሮ ኣይግባ*።

☐ ወደ የቀድሞ ስሜ ይመልሱኝ።

**ፍርድ ቤቱ ፍትሐዊና ተገቢ ነው ያለውን ሌላ ማንኛውንም እፎይዳ <u>እንዲሰጠኝ ደግሞ</u> እጠይቃለሁኝ።**

[በአንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]
☐ ይህንን ማመልከቻ ወይም ጉዳይ የሚመለከት፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ወይም በሌላ የሆነ ክልል ውስጥ የሚካሄድ የሆነ ሂደት መኖሩን *አላውቅም*።

☐ ይህንን ማመልከቻ ወይም ጉዳይ የሚመለከት፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ወይም በሌላ ስቴት ውስጥ የሚካሄድ የሆነ ሂደት መኖሩን *አውቃለሁኝ*፡ ጉዳዩም በዚህ የክስ ወረቀት (“ተዛማጅ ጉዳዮች”) በመጀመሪያ ገጽ ላይ ተገልጿል።

የሐሰት ቃል ከሰጠሁኝ የወንጀል መቀጮ እንደማገኝ እያወቅሁኝ፣ ይህንን ጋብቻን ለማፍረስ የቀረበ ክስ እንዳነበብኩትና፣ በውስጡ የተጠቀሱት ቃላት፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ባለኝ መረጃና እምነት መሰረት እውነት መሆኑን የእምነት ቃሌን እሰጣለሁኝ።

ከአክብሮት ጋራ አስገቢ፣

______________________________
ስምዎን ይፈርሙ

______________________________
ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)

______________________________
የጎዳና አድራሻ

______________________________
ከተማ፣ ስቴት እና ዚፕ ኮድ

______________________________
የስልክ ቁጥር

____________________
ኢሜይል አድራሻ

☐ ተተኪ አድራሻ፤ ንዝነዛ ወይም ጉዳትን ፈርተው የሌላን ሰው አድራሻ ጽፈው ከሆነ በሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።

**መመሪያ 4**
**መጥሪያ ስለመድረሱ የምስክር ወረቀት**

የክስ ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የማመልከቻ መቀበያ ማእከል (FAMILY COURT CENTRAL INTAKE CENTER) ለሌላኛው ወገን ማድረስ ያለብዎትን፣ ያስገቡት የክስ ግልባጭ የያዘ **መጥሪያ** (**SUMMONS**) ይሰጥዎታል።

መጥሪያው በ 60 ቀን ውስጥ ከመቃጠሉ በፊት ለሌላኛው ወገን ማድረስ ይኖርብዎታል።

ለሌላኛው ወገን በ 60 ቀኖች ውስጥ ማድረስ ካልቻሉ፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የማመልከቻ መቀበያ ማእከሉን ሌላ መጥሪያ እንዲሰጥዎ ሊጠይቁት ይችላሉ። ሁለተኛው መጥሪያ "አሊያስ ሳመንስ" ("ALIAS SUMMONS") ተብሎ ይጠራል። የመጀመሪያው መጥሪያ ከመቃጠሉ **በፊት** ይህ እንዲሰጥዎ መጠየቅ **ይኖርብዎታል**።

ክስዎንና መጥሪያውን የሚያደርሱባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፤

- **ሌላ ሰው**፣ ዕድሜው 18 ዓመት የሞላውና ይህ ጉዳይ የማይመለከተው (እርስዎ አይሆኑም) ፣ **ለሌላኛው ወገን በእጅ እዲሰጡ ማድረግ**፣ ወይም
- **ሌላ ሰው** ዕድሜው 18 ዓመት የሞላውና ይህ ጉዳይ የማይመለከተው (እርስዎ አይሆኑም) ፣ በሌላኛው ወገን ጋራ አብሮ ከሚኖር፣ ተገቢ ዕድሜና ሁኔታ ያለው ሰው ጋራ፣ **ግልባጩን በሌላኛው ወገን ቤት ውስጥ መተው**፣ ወይም
- **በፖስታ ወደ ሌላኛው ወገን**፣ በአደራ ደብዳቤ፣ መድረሱን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ያለው።

  መድረዱን የሚያረጋግጠው ደረሰኝ ("GREEN CARD") ፣ ወደ እርስዎ ተመልሶ ሲመጣ፣ ወደ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የማመልከቻ መቀበያ ማእከል (FAMILY COURT CENTRAL INTAKE CENTER) ከ "AFFIDAVIT OF RETURN OF SERVICE BY CERTIFIED MAIL" ጋራ አንድ ላይ አያይዘው ያስገቡ።

**ወደ ሌላኛ ወገን ካደረሱት በኋላ፣ በመጥሪያው የታችኛው ክፍል ላይ የሚገኘውን መጥሪያ የማድረስ የምስክር ወረቀት (CERTIFICATE OF SERVICE) ክፍሉን ሞልተው ወደ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የማመልከቻ መቀበያ ማእከል (FAMILY COURT CENTRAL INTAKE CENTER) ያስገቡ።**

Translated by JTG, Inc. 05/2017